# ጓደኝነትና የአንድን ሰው ማንነት በማዋቀር ያለው ተጽእኖ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{الْأَخِلَّاءُ يَوْمَئِذٍ بَعْضُهُمْ لِبَعْضٍ عَدُوٌّ إِلَّا الْمُتَّقِينَ}
ለአለው ለዐለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (ወዳጆች በዚያን ቀን ከፊላቸው ለከፊሉ ጠላት ነው፡፡ አላህን ፈሪዎች ብቻ ሲቀሩ፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ማህበራዊ ፍጡር ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ሲኖር ከሌላው ሰው በሚለየው የማንነት ባሕርዩ አማካይነት የማህበረሰቡ ተጽእኖ ያድርበታል፡፡ እንድሁም ከሱ ጋር የጋራ እንቅስቃሴዎችን ያከናውናል፡፡ አብሮ መኖርና ጓደኝነት በአንድ ሰው እሳቦትና ስርአተ ሕይወት ግልጽ የሆነ ተጽእኖ አላቸው፡፡ በእነሱም አማካይነት የአንድ ሰው የወደፊት እጣፋንታዎና በዚህች ዓለምም ሆነ በመጭው ዓለም የሚኖረው ደስታ ይወሰናል፡፡
የሚገነባና የማያፈርስ፣ የሚያለማና የማያበላሽ እንድሁም ከማንኛውም ሌላ ጥቅም አጠቃላይ የሀገርን ጥቅም የሚያስቀድም ትውልድ ለማዘጋጀት በታላቅ ሰብእነትና በከፍተኛ ሐገራዊ ፍቅር ደረጃ የታነጸ ትክክለኛ ማንነት የሚያስፈልገን መሆኑ አያነጋግርም፡፡
ቅኑ የእስልምና ህግ አደጋን ፈጥኖ የሚረዳ ሙሉ ግንዛቤ ያለውና የህይወትን ችግሮች በተገቢው መልኩ የሚቋቋም እንድሁም መከራዎችንና አጠራጣሪ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያልፍ ማንነት ያለው ግለሰብ መገንባት መስፈርቱን አሟልቶ እንድከናወን አዟል፡፡
አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡
{وَاتَّقُوا فِتْنَةً لَّا تُصِيبَنَّ الَّذِينَ ظَلَمُوا مِنكُمْ خَاصَّةً }

ትርጉሙም (ያችን እነዚያን የበደሉት ሰዎች ብቻ የማትነካን ፈተና ተጠንቀቁ፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህው የእስልምና ህግ ማንኛውም ሰው ጠቃሚ ቀጥተኛ መንገድን የሚረዳ፣ እውነትን የሚከተልና ከጭፍን ተጓዦች ጋር አብሮ የማይነጉድ የማያውላውል በራሱ መተማመንን መሰረት ያደረገ ማንነት እንድኖረው መምሪያ ሰጥቷል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ሰዎች መልካም ሲሠሩ መልከም እንሠራለን ከበደሉም እንበድላለን የምትሉ አብሮ ነጓጅ አትሁኑ፡፡ ነገር ግን ሰዎች መልካም ሲሠሩ መልካም በመስራትና ሲበድሉ ባለመበደል መንፈሳችሁን ግሯት፡፡)

የአንድን ሰው ማንነት በማዋቀር ረገድ ጥልቅ ተጽእኖ ካለቸው አበይት ነገሮች አንደኛው ጓደኝነት መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡ አንድ ሰው አቀማማጩ ትጽእኖ ያሳድርበታል እንድሁም በእሳቦት፣በእምነት፣ በስነ ምግባርና በስራ የሱን ገጽታ ይይዛል፡፡ ይህ ጉዳይ በህግ፣ በአአምሮ፣ በተሞክሮ፣ በተጨባጭ ነገሮችና በምልከታ ተረጋግጧል፡፡

እዚህ ላይ እንግድህ የመልካም ጓደኝነት አስፈላጊነት ለሃይማኖቱ፣ ለሀገሩና ለማህበረሰቡ ጠቃሚ የሆንን ትክክለኛ ማንነት በመዋቀር ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ ነው እንላለን፡፡ በዚህም ሁኔታ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.)የተከበሩ ባልደረቦቻቸውን አስተምረዋል፡፡ ከነሱም መካከል በቀደምትነት የሚጠቀሱት (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) በመልካም ጓደኝነት አርኣያነት ያለው ተግባር የፈጸሙትና የምልካም ጓደኝነትን ሙሉ መብት ያደረሱት አቡ በክር አል ሲዲቅ ናቸው፡፡ ይህም የመካ ሰዎች ይህ ባልደረባህ ዛሬ ሌሊት ወደበይተል መቅድስ ሄዶ ከዚያም እንደተመለሰ ያወራል ባሉ ጊዜ በጓደኛቸው ያለቸውን ሙሉ እምነት በማጉላትና በእርግጠኝነት ‹እንደዚህ በለው ከሆነ በእርግጥም እውነት ተናግረዋል፡፡ አኔ ከዚያ በራቀ ነገር አምናቸዋለሁ በሰማይ ወሬ› በማለታቸው ነው፡፡

ይህ ተግባር የነብያችን ባልደረቦች (ሶ.ዐ.ወ.) ከመካከላቸው ሲያከናዉነት የኖረ ተግባር ነው፡፡ እነሱም በወንድም ተማማችነት፣ ከራስ ሰዎችን በማስቀደም፣ በአንድነት፣ ጠቃሚ በሆነ አዎንታዊ ሥራ በመዋደድና በመተዛዘን የታነጸ ደግ የሆነ መልካም ጓደንነት ልንከተለው የሚገባ አርኣያ ናቸው፡፡ ኑዕማን ኢብን በሺር እንድህ ብለዋል፡ ‹የአላህ መልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (ምእምናን በመዋደዳቸው፣ በመተዛዘናቸውና እንዱ ለሌላው በመጨነቃቸው አንድ የአካል ክፍል ህመም በተሰማው ጊዜ ሌሎቹም አካላት እንቅልፍ በማጣትና በመሰቃየት እንደሚጠራሩለት አንድ ሰውነት ናቸው፡፡)

እንድሁም የጻድቃን ጓደኝነት በዚህችም ዓለም ሆነ በመጭው ዓለም ልዩ በረከትና ትሩፋት ያለው መሆኑን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጠዋል፡ (የበረከት ባለቤትና ታላቅ ለሆነው አላህ የተከበሩ በራሪ መላእኮች አሉት፡፡ አነሱም አላህን ማስታወስ ያለባቸውን የሰዎች ስብስብ ይከታተላሉ፡፡ አንድ አላህ የሚወሳበትን ስብስብ ሲያገኙ አነሱ ጋር ይቀመጣሉ፡፡ ከፊላቸው በከፊላቸው ክንፍ ከነሱና ከመድር ሽፋን ሰማይ መካከል ያለውን ቦታ ይሸፍናሉ፡፡ ሲበታተኑም ተነስተው ወደሰማይ ያርጋሉ፡፡ ከዚያም እንድህ አሉ፡ አላህ (ዐ.ወ.) የነሱን ሁኔታ እያወቀ ሳለ ከየት

መጣችሁ ብሎ ይጠይቃቸዋል፡፡ አነሱም እኛ የመጣነው በምድር ከሚኖሩ ለአንተ ከሆኑ ባሮች ዘንድ ነው፡፡ እነሱም ያጠሩሃል፣ ታላቅነትህን ይናገራሉ፣ ካንተ በስተቀር አምላክ እንደሌለም ይመሰክራሉ፣ ያመሰግኑሃል ይለምኑሃልም ይላሉ፡፡ እሱም ምንድነው የሚለምኑኝ? ሲል ይጠይቃቸወል፡፡ እነሱም ጀነተህን ነው የሚለምኑህ ይላሉ፡፡ እሱም ጀነቴን አይተዋል እንዴ? በማለት ይጠይቃቸዋል፡፡ እነሱም አላዩአትም ጌታችን ሆይ! ይላሉ፡፡ እሱም ጀነቴን በዩዋት ኖሮ እንደት ይሆኑ ነበር? ይላል፡፡ እነሱም ካንትም ጥበቃን ይጠይቃሉ ይላሉ፡፡ እሱም ከምን እንዲጠብቃቸው ነው የሚጠይቁት? ይላል፡፡ እነሱም ጌታችን ሆይ! ከእሳትህ እንዲትጠብቃቸው ነው የሚጠይቁህ ይላሉ፡፡ እሱም እሳቴን አይተዋታል እንዴ? ሲል ይጠይቃቸዋል፡፡ እነሱም አላየዋትም ጌታችን ሆይ! እሱም ቢያዩዋት ኖሮ እንዴት ይሆኑ ነበር ይላል፡፡ እነሱም ምህረትንም ይጠይቁሃል ይላሉ፡፡ እሱም በእርግጥ ምህረት አድርጌላቸዋለሁ፣ የለመኑትንም ስጥቻቸዋለሁ፣ እንድጠብቃቸው ከጠየቀኝም ነገር ጠብቂያቸዋለሁ፣ ከዚያም ነብያችን እንድህ አሉ እነሱ እንድህ ይላሉ፡ ጌታችን ሆይ! ስህተት ፈጻሚው አገሌኮ ከነሱ መካከል አለ እሱም በዚያ ሲያልፍ ነው ከነሱ ጋር የተቀመጠው ይላሉ፡፡ እሱም ለሱም ምህረት አድርገሁ አነሱ አቀማማጫቸው መናጢ የማይሆን ሰዎች ናቸውና፡፡)

ከመልካም ጓደኝነት ጥቅም አንደኛው የአላህን ውዴታ እንድሁም ጀነትን የሚያስገኝ መሆኑ ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራህ የተባሉት ባልደረባ እንድህ ብለዋል፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (አንድ ሰው በሌላ መንደር የሚኖር ወንድሙን ሊጠይቅ ሄደ በመንገዱ ላይ መላእክ አስቀመጠለት ወደሱ በደረሰ ጊዜ ወዴት እየሄድህ ነው? ሲል ጠየቀው፡፡ እሱም እዚህች መንደር ያለን ወንድሜን ለመጠየቅ ነው አለ፡፡ ከሱ የምታገኘው ጥቅም አላህን? በማለት ጠየቀው፡፡ እሱም የለም ነገር ግን ለአላህ ብዬ የወደድሁት ወንድሜ ነው፡፡ መላእኩም አኔ ወዳንተ የተላከሁ መልከተኛ ነኝ፡፡ አላህ ለሱ ብለህ ወንድምህን እንደወደድህ ሁሉ አላህ ወዶሃል አለው፡፡)

እንደዚሁም መልካም ጓደኝነት በትንሳኤ ቀን ከመልካሞቹ ጋር መሰብሰብን ያስገኛል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድን) አነስ ኢብን ማሊክ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹አንድ ሰውዬ መቼ ነው የትንሳኤ ቀን ሲል ስለትንሳኤ ቀን ነብያችንን (ሰ.ዐ.ወ.) ጠየቀ፡፡ እሳቸውም (ለሱ ምን አዘጋጅተህላታል?) ሲሉ ጠየቁት፡፡ እሱም ምንም አለዘጋጀሁም ነገር ግን አላህንና መልከተኛውን እወዳለሁ አለ፡፡ እሳቸውም (አንተ ከወደድከው ጋር ነህ፡፡) አሉት፡፡ አነሱም ያን ጊዜ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ‹አንተ ከወደድከው ጋር ነው› በማለታቸው የተደሰትነውን ያህል ተደስተን አናውቅም› አሉ፡፡ አነሱም አኔ የአላህን መልከተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)ን፣ አቡ በክር ሲዲቅንና ዑመርን እወዳለሁ አነሱን በመውደዴም ከነሱ ጋር መሆንን ተስፋ አደርጋለሁ የንሱን ዓይነት ሥራ ባልሰራም እንኳ አሉ፡፡›

ኢማሙ አሻፊዒ የተባሉት ሊቅ እንድህ በማለታቸው ይደነቃሉ፡

ከነሱ አይደለሁም ጻድቃንን እወዳቸዋለሁ፡፡ በነሱ ምናልባት መታደግን እከጅላለሁ፡፡
በወንጅል የሚነግድን ሰው እጠላለሁ፡፡ በእቃ ከነሱ ጋር እኩል በንሆንም እንኳ፡፤

ከጻድቃን ጓደኝነት ጥቅሞች ሌላው ደግሞ አላህን እንድናስታውስ ያደርገናል እንድሁም በተለያዩ ዘርፎች በዚህችም ዓለምም ሆነ በመጭው ዓለም በርካታ መልካም ነገሮችን ያስገኛል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን ዓባስ የተባሉት ባልደረባ እንድህ ብለዋል፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ያላህ መልክተኛ ሆይ! የትኛው አቀማማጭ ነው መልካሙ የሚል ጥያቄ ተጠየቁ እሳቸውም (ስታዩት አላህን እንድታስታውሱ፣ ንግግሩ እውቀታችሁን እንድትጨምሩ፣ ሥራው መጭውን ዓለም የሚያስታውሳችሁ ነው፡፡)

ትክክለኛ ጓደኛ የወንድሙ መስተዋት ነው፡፡ ወደመልካምም ነገር ይመራል፡፡ ከተንኮልም ይከልክላል፡፡ ለራሱ የሚወደን ለወንድም እንድወድ ያደርጋል፡፡ አላህ እንድህ ይላል፡

{وَالْعَصْرِ *إِنَّ الْإِنْسَانَ لَفِي خُسْرٍ *إِلَّا الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ وَتَوَاصَوْا بِالْحَقِّ وَتَوَاصَوْا بِالصَّبْرِ}

ትርጉሙም (በግዚያቱ እምላለሁ፡፡ ሰዎች ሁሉ በእርግጥ በኪሳራ ላይ ናቸው፡፡ እነዚያ መኑት መልካሞችን የሡሩት በእውነት አደራ የተባባሉት በትግስትም አደራ የተባበሉት ብቻ ሲቀሩ፡፡) ማለት ነው፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አነስ ኢብን ማሊክ እንድህ ብለዋል፡ አላህ መልክተኛ እንድህ አሉ፡ (ወንድምህን በዳይም ይሁን ተበዳይ እርዳ፡፡) አሉ፡፡ እኛም ያለህ መልክተኛ ሆይ! ተበደይ ሲሆን እንረደዋለን በዳይ ሲሆን እንደት እነረደዋለን አልን፡፡ እሳቸውም (ከበደል ታግደዋለህ ይህም ለሱ የምታደርገው እርዳታ ነው፡፡) አሉ፡፡

ይህን መሰረት በማድረግ መልካሙ ጓደኛ ጓደኛው ከቀጥተኛ መስመር በወጣና ጀመረ ጊዜ ምክሩን ይለግሰዋል፣ እውነቱንም ያብራራለታል፣ መስራት ያለበትንም ነገር ይግልጽለታል፣ ከአላህ መራቅ የሚያስከትለውንም ችግር ያስጠነቅቀዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{قَالَ لَهُ صَاحِبُهُ وَهُوَ يُحَاوِرُهُ أَكَفَرْتَ بِالَّذِي خَلَقَكَ مِن تُرَابٍ ثُمَّ مِن نُّطْفَةٍ ثُمَّ سَوَّاكَ رَجُلًا *لَّكِنَّا هُوَ اللَّهُ رَبِّي وَلَا أُشْرِكُ بِرَبِّي أَحَدًا *وَلَوْلَا إِذْ دَخَلْتَ جَنَّتَكَ قُلْتَ مَا شَاءَ اللَّهُ لَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللَّهِ إِن تَرَنِ أَنَا أَقَلَّ مِنكَ مَالًا وَوَلَدًا * فَعَسَى رَبِّي أَن يُؤْتِيَنِ خَيْرًا مِّن جَنَّتِكَ وَيُرْسِلَ عَلَيْهَا حُسْبَانًا مِّنَ السَّمَاءِ فَتُصْبِحَ صَعِيدًا زَلَقًا *أَوْ يُصْبِحَ مَاؤُهَا غَوْرًا فَلَن تَسْتَطِيعَ لَهُ طَلَبًا *وَأُحِيطَ بِثَمَرِهِ فَأَصْبَحَ يُقَلِّبُ كَفَّيْهِ عَلَى مَا أَنفَقَ فِيهَا وَهِيَ خَاوِيَةٌ عَلَى عُرُوشِهَا وَيَقُولُ يَا لَيْتَنِي لَمْ أُشْرِكْ بِرَبِّي أَحَدًا}.

ትርጉሙም (ጓደኛው (አማኙ) እርሱ ለርሱ የሚመላለሰው ሲሆን በዚያ ከአፈር ከዚያም ከፍተወት ጠብታ ከፈጠረህ ከዚያም ሰው ባደረግህ (አምላክ) ካድክን? አለው፡፡ እኔ ግን እርሱ አላህ ጌታዬ ነው (እላለሁ)፡፡ በጌታየም አንድንም አላጋራም፡፡ አትክልትህም በገባህ ጊዜ አላህ የሻው ይሆናል በአላህ ቢሆን እንጂ ሃይል የለም

አትልም ኖሯልን? እኔን በሃብትም በልጅም ካንተ በጣም ያነስኩ ሆኜ ብታየኝ ጌታየ ከአትክልትህ የበለጠን ሊሰጠኝ በርሷም (በአትክልትህ) ላይ ከሰማይ መብረቆችን ሊልክባትና የምታንዳልጥ ምልጥ ምድር ልትሆን ይችላል፡፡ ወይም ውሃ ሰራጊ ሊሆን ይችላል፡፡ ያን ጊዜ ለርሱ መፈለግን ፈጽሞ አትችልም (አለው) ሀብቱም ጠፉ እሷ በዳሶቿ ላይ የወደቀች ሆና በእርሷ ባወጣው ገንዘብ ላይ (እየተጸጸተ) መዳፎቹን የሚያገላብጥና ወይ ጸጸቴ በጌታዬ አንድም ባላጋራሁ የሚል ሆኖ ለእርሱም ከአላህ ሌላ የሚረዱት ጭፍሮች አልነበሩትም፡፡) ማለት ነው፡፡

እንድህ ያለው ገጣሚ እንድህ በማለቱ በጣም ይደነቃል፡

ትክክልኛ ወንድምህ ካንተ ጋር የሚሆን ነው፡፡ አንተን ሊጠቅምም ራሱን የሚጎዳው፡፡ ቀን በጣለህም ጊዜ አንተን ሊሰበስብህ አራሱን ይበታትናል፡፡

ለመልካም ጓደኝነት በዚህም ዓለም ይሁን በመጭው ዓለም መልካምና ጠቃሚ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ሁሉ አፍራሽና መስመር ሳች አሉታዊ ማንነት በማዋቀር መጥፎ ጓደንነት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

በመሆኑም በዚህች ዓለም ጎጂና አበላሽ ተጽእኖ በመጭውም ዓለም ኪሳራ ያደርሳል፡፡ መጥፎ ጓደኝነት መልካም እሴቶችን ያፈርሳል፡፡ መልካም ምግባራትን ያብሳል፡፡ እንድሁም ታዳጊውንም ይሁን ወጣቱን ያበላሻል፡፡ ሥራን ያስተጓጉላል፡፡ አሉባልታና ጥሜት ይስፋፋል፡፡ መጥፎ ሰሪ ጓደኛው እምነትን በማበላሸት፣ አፍራሽ እሳቦትን በማስፋፋት መጥፎ እንድስራ ይጥራል፡፡ የመጥፎ ጓደኝነትን ገጽታ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጾታል፡

{فَأَقْبَلَ بَعْضُهُمْ عَلَى بَعْضٍ يَتَسَاءَلُونَ * قَالَ قَائِلٌ مِنْهُمْ إِنِّي كَانَ لِي قَرِينٌ *يَقُولُ أَإِنَّكَ لَمِنَ الْمُصَدِّقِينَ *أَإِذَا مِتْنَا وَكُنَّا تُرَابًا وَعِظَامًا أَإِنَّا لَمَدِينُونَ * قَالَ هَلْ أَنْتُمْ مُطَّلِعُونَ * فَاطَّلَعَ فَرَآهُ فِي سَوَاءِ الْجَحِيمِ *قَالَ تَاللَّهِ إِنْ كِدْتَ لَتُرْدِينِ *وَلَوْلَا نِعْمَةُ رَبِّي لَكُنْتُ مِنَ الْمُحْضَرِينَ *أَفَمَا نَحْنُ بِمَيِّتِينَ *إِلَّا مَوْتَتَنَا الْأُولَى وَمَا نَحْنُ بِمُعَذَّبِينَ *إِنَّ هَذَا لَهُوَ الْفَوْزُ الْعَظِيمُ * لِمِثْلِ هَذَا فَلْيَعْمَلِ الْعَامِلُونَ}

ትርጉሙም (የሚጠያየቁም ሆነው ከፊላቸው ወደከፊላቸው ይመጣሉ፡፡ ከነርሱ የሆነ ተናጋሪ ይላል እኔ ጓደኛ ነበረኝ፡፡ በእርግጥ አንተ ከሚያምኑት ነህን? የሚል፡፡ በሞትንና አፈር አጥንቶች በሆን ጊዜ እኛ በርግጥ እንመረመራለን? የሚል፡፡ እናንተ ተመልካቾች ናችሁን? ይላል፡፡ ይመለከታልም በገሀነም መካከልም (ጓደኛውን) ያየዋል ይላል በአላህ እምላለሁ፡፡ በእርግጥ ልታጠፋኝ ቀርበህ ነበር የጌታየም ጸጋ ባይኖር ኖሮ ወደእሳት የምቀርብ እሆን ነበር፡፡ እኛ የምንሞት አይደለንምን የመጀመሪያውን ሞታችንን እንጂ እኛም የምንቀጣ አይደለንምን፡፡ ይህ ታላቅ ስኬት ነው፡፡ ለዚህም አምሳያ ሰሪዎች ይስሩ፡፡) መለት ነው፡፡

{وَيَوْمَ يَعَضُّ الظَّالِمُ عَلَى يَدَيْهِ يَقُولُ يَا لَيْتَنِي اتَّخَذْتُ مَعَ الرَّسُولِ سَبِيلًا *يَا وَيْلَتَى لَيْتَنِي لَمْ أَتَّخِذْ فُلَانًا خَلِيلًا *لَقَدْ أَضَلَّنِي عَنِ الذِّكْرِ بَعْدَ إِذْ جَاءَنِي وَكَانَ الشَّيْطَانُ لِلْإِنْسَانِ خَذُولًا}

ትርጉሙም (በዳይም ከመልክተኛው ጋር ቀትኛውን መንገድ ይዤ በሆነ ዋ ምኞቴ እያለ (በጸጸት) ሁለት እጆቹን የሚነክስበትን ቀን (አስታውስ) ማለት ነው፡፡ ዋ ጥፋቴ እገሌን ወዳጅ ባልያዝኩ ኖሮ እመኛለሁ፡፡ (የእመነት ቃልን) ከመጣልኝ በኋላ

ከማስታወስ በእርግጥ አሳሳተኝ፡፡ (ይላል) ሰይጣንም ለሰው አጋላጭ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መጥፎ ጓደኝነት ወናፍ እንደሚነፋ ሰው መሆኑን እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (የመልካም አቀማማጭና የመጥፎ አቀማማጭ ምሳሌ እንደሚስክ ተሸካሚና እንደወናፍ ነፊ ነው፡፡ ሚስክ ተሸካሚ ወይም በሽታው ይስበሃል ወይም ከሱ ትገዛለህ፡፡ ወይም ከሱ መልካም ሽታ ታገኛለህ፡፡ ወናፍ ነፊ ደግሞ ጨርቅህን ያቃጥልለሃል ወይም መጥፎ ሽታ ያስከትልብሃል፡፡)

መጥፎ ጓደኝነት ራስን እንድሁም ሌላን ለመበደል በር ይከፍታል፡፡ እንድሁም ወደአፍራሽና በምድር አበላሽ ቡድኖች ጎዳናም ይመራል፡፡ እንድሁም ወደአደንዛዥ እጽና ወደሱስ የሚያደርስ ሲሆን ማንኛውንም ሰው በዚህች ዓለምም ሆነ በመጭው ዓለም ወደጥፋትና አላህ ወደሚጠላው ነገር ይመራል፡፡

ይህን ነገር ተናገርሁኝ ለኔና ከናንተ ከአላህ ዘንድ ምህረትን እጠይቃለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

እኛ ሁላችንም ከመጥፎ ሰዎች መጠንቀቅና ከነሱ ጋር አለመቀላቀል ይኖርብናል፡፡አላህ (ሱ.ዐ.) እንድህ ይላል፡

{وَقَدْ نَزَّلَ عَلَيْكُمْ فِي الْكِتَابِ أَنْ إِذَا سَمِعْتُمْ آيَاتِ اللَّهِ يُكْفَرُ بِهَا وَيُسْتَهْزَأُ بِهَا فَلَا تَقْعُدُوا مَعَهُمْ حَتَّىٰ يَخُوضُوا فِي حَدِيثٍ غَيْرِهِ إِنَّكُمْ إِذًا مِثْلُهُمْ إِنَّ اللَّهَ جَامِعُ الْمُنَافِقِينَ وَالْكَافِرِينَ فِي جَهَنَّمَ جَمِيعًا}

ትርጉሙም (በእናንተም ላይ በመጽሐፉ ውስጥ የአላህን አንቀጾች በርሷ ሲካድባትና በርሷ ሲላገጥባት በሰማችሁ ጊዜ በሌላ ወሬ ውስጥ እስከሚገቡ ድረስ ከነሱ ጋር አትቀመጡ፡፡ ማለትን በእርግጥ አወረደ፡፡ እናንተ በዚያን ጊዜ በጥያቸው ናችሁ፡፡ አላህ ምናፍቃንን እና ከሃደዎችን በሙሉ በገሀነም ውስጥ ሰብሳቢ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡

{وَإِذَا رَأَيْتَ الَّذِينَ يَخُوضُونَ فِي آيَاتِنَا فَأَعْرِضْ عَنْهُمْ حَتَّىٰ يَخُوضُوا فِي حَدِيثٍ غَيْرِهِ وَإِمَّا يُنْسِيَنَّكَ الشَّيْطَانُ فَلَا تَقْعُدْ بَعْدَ الذِّكْرَىٰ مَعَ الْقَوْمِ الظَّالِمِينَ}

ትርጉሙም (እነዚያን በአንቀጾቻችን የሚገቡትን ባየህ ጊዜ ከእርሱ ሌላ በሆነ ወሬ እስከሚገቡ ድረስ ተዋቸው ፡፡ ሰይጣንም (መከልከልህን) ቢያስረሳህ ከትውስታ በኋላ ከበደለኞች ጋር አትቀመጥ፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሰው በወዳጁ ሃይማኖት ይመራልና አንዳችሁ ማነን እንደሚወዳጅ መገምገም አለበት፡፡) እንድሁም እንድህ ይላሉ፡ (ምእምንን እንጂ ጓደኛ አታድርግ፡፡ መግብህንም አላህን የሚፈራ እንጂ አይብላ፡፡) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አብደላህ ኢብን ማስዑድ እንድህ ብለዋል፡ ‹ሰዎችን በወዳጆቻቸው ገምግሙ አንድ ሰው የሚደንቀውን እንጂ ወዳጅ አያደርግም፡፡›
እንድህ የሚለው ግጥም ደራሲ እጇጉን ይደነቃል፡
በአንድ ህዝብ ውስጥ የምትኖር ከሆነ ምርጣቸውን ወዳጅ አድርግ፡፡ ዝቅተኛውን አትወዳጅ አብረህ እርኩስ ተኋናለህና፡፡
ስለአንድ ሰው አትጠይቅ ነገር ግን ስለጓደኛው ጠይቅ፡፡ አንድ ሰው ጓደኛውን ይከተላልና፡፡
እዚህ ላይ በመልካም ጓደኝነት አማካይነት ማንነትን ማዋቀር ማህበረሰቡ ሁሉ ሊረባረብበት የሚገባ የጋራ ሃላፊነትን የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑን ማረጋገጥ እንወዳለን፡፡ ሁሉም የማህበረሰቡ አባል ይህ ሃላፊነት እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ሊገነዘብ ይገባል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሁላችሁም ጠባቂዎች ናችሁ ሁላችሁም ስለሚጠብቁት ነገር ሁሉ ይጠየቃል፡፡ አንድ መሪ ስለህዝቡ ተጠያቂ ነው፡፡ አንድ ሰው ቤተሰቡን ይጠብቃል እሱም ስለሚጠብቀው ነገር ይጠያቃል፡፡ ሴትም የባሏን ቤት ትጠብቃለች እሷም ስለምትጠብቀው ተጠያቂ ናት፡፡ አገልጋይ የጌታውን ገንዘብ ይጠብቃል እሱም ስለሚጠብቀው ነገር ይጠየቃል፡፡)
ታዳጊዎችን በማስተማርና በመጠበቅ በቤተሰብ በትምህርት ቤት እንድሁም በትምህርታዊና ምርምራዊ የማህበራዊ ደርጅቶች፣ በማስታወቂያ ተቋማት አማካይነት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡ እንድህም ታዳጊዎችን አፍራሽ ከሆነው ከጸንፈኛና አታላይ ቡድኖች አስተሳሰብ ለመጠበቅ የሀገር ፍቅር ለማጽረጽ ሁሉም ወገን መረባረብ ይጠበቅበታል፡፡ ታዳጊዎችን በሚገባው መልኩ መጠበቅ ታላቅ ሃላፊነት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا قُوا أَنفُسَكُمْ وَأَهْلِيكُمْ نَارًا}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ራሳችሁንና ቤተሰቦቻችሁንም ከእሳት ጠብቁ፡፡) ማለት፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አላህ ጠባቂን ከሚጠብቀው ነገር ጠብቋል ወይስ አጥፍቷል በማለት ጠያቂ ነው፡፡ አንድን ሰው ከቤተሰቡም እንኳ ይጠይቀዋል፡፡)
ጌታችን ሆይ መልካም ጓደኛን ስጠን፡፡ የአለማቱ ጌታ ሆይ የመልካም ጓደኝነትን ፍሬ እውን አድርግልን፡፡